★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 36 ቁጥር 5 የካቲት 2003 ዓ.ም

## የካቲት ሲታወስ፣ ሃገር በአምባገነን ዘረኛ ቡድን ሲታመስ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጫንቃው ላይ ተኮፍሰው ሳያሰልሱ ለዘመናት ሲበዘብዙትና ሲጨቁኑት የቆዩትን ኢ-ፍትሃዊ አገዛዞች ለመገርሰስ በልዩ ልዩ ወቅትና በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ አመጾች- የአርሶ አደሮች፣ የላብ አደሮች፣ የመምህራን፣ የተማሪዎች ባጠቃላይም የሰፊው ጭቁን ሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች - አንዴ ሞቅ አንዴ ቀዝቀዝ እያሉ እያደርም በአንዳንድ ቦታዎች በትጥቅ ጭምር እየታጀቡ የተካሄዱ ቢሆንም፣ በጊዜው በቂ አደረጃጀት ያልነበራቸውና በተናጠል ይደረጉ ስለነበር፤ ሁሌም ለአገዛዙ ሰለባ በመሆን አንድ በአንድ እንዲከሽፉ እየተደረጉበት እንደነበር የሚታወስ ነው። የግፉና የመከራው ጽዋ ከእንግዲህስ ያብቃ የሚለው ታላቁ የለውጥ ደወል የብሩህ ተስፋ ምሥራቹን ለተገፋው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰሜን እስከደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከምዕራብ በማብሰር የናጠጠው መሳፍንታዊ አገዛዝ ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ምድር ማክተሙን ለዓለም ሁሉ ይፋ ያደረገው የወርሃ የካቲት ግብታዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ከአስገመገመ እነሆ ሰላሳ ሰባት ዓመታትን አስቆጠረ።

የሰማዕታቱ መታሰቢያ ወር የሆነው የካቲት የኢትዮጵያን ምድር ሳይታሰብ በለውጥ እንቅስቃሴ ናጠው። ለቅሶና ዋይታ፣ የቆሙበት መሬት መራድ፣ እዬዬና መኮራመት የዘወትር ቦታቸውን ለቀው በቅምጥሎች ሰፈር ገዘፉ፤ መፈንደቅ፣ ፈካ ፈካ ማለትና የደስታ መንፈስ ተስተናግደውበት በማያቁበት መንደር ድንገት ገብተው የብዙ ሚሊዮን ጭቁን ነፍሶችን በብሩህ ተስፋ ሞሏቸው። በኢትዮጵያ ምድር በዚያችው ባንድ አገር ውስጥ በአንድ ሕዝብ መካከል እልልታም ኡኡታም፤ ሃዘንም ደስታም ምድሪቱን ሞሏት። በርግጥም አርድ አንቀጥቅጥ ሁኔታ!

የኢትዮጵያ ጭቁን አርሶ አደሮች ለዘመናት የጉልተኛው ሥርዓት ሲያደርስባቸው የነበረውን አስከፊ ጭቆናና በደል በመቃወም ሲታገሉት የቆዩ ቢሆንም ሥርዓቱ የሕዝቡን ተቃውሞ ከቁጥር አስገብቶ እህ ብሎ ያዳመጠበት ሁኔታ ሳይሆን ይብሱኑ በላይ በላዩ ሳያሰልስ ግፉን በመቀጠሉ ጭቁኑ ሕዝብ ከሰውነት ውጪ እንዲሆን አደረገ። የጭሰኝነቱ ኑሮ እጅጉን አስከፊና መራር ስለነበር፣ ገፈቱን ቀማሽ የሆነው አርሶ አደር አገሩ ሲኦል ሆናበት በውል የሚያደርገውና የሚሆነው ጠፍቶበት "ተው ስማኝ

ሃገሬ፤ እረ ስማኝ ሃገሬ"-ን ነጋ ጠባ እንዲያቀነቅን ተገደደ። አርሶ አደሩ ዓመት ሙሉ ሌት ተቀን ሲማስን የደከመበትን ጥሪት፣ ሙክቱን፣ ቅቤውን፣ ማሩን፣ ...ወዘተ ለቅምጥሉ የመሬት ባለቤት የማስረከቡ አዙሪት አላባራ ብሎ ትውልድ አልፎ ትውልድ ቢተካም ነገረ ሥራው ሁሉ ዛሬም እዛው ነሽ ወይ ዓይነት ሆኖበት፣ የመኖር ትርጉሙ እጅ እጅ ሲለው ኖሯል። በዚያ ዘግናኝ ዘመን፣ የሚያርሰው መሬት ባለቤት የሚሆንበትን፣ ምርቱን ገበያው በተመነው መጠን ሊሸጥ ሊለውጥ የሚችልበትን፣ ጤንነቱ የሚጠበቅበትን፣ ልጆቹ ትምህርት የሚቀስሙበትን፣ ንጹህ ውሃ፣ መብራት፣ መንገድ የመሳሰሉት ሁሉ እውን የሚሆኑበትን ጊዜ መቃረቡን የሚያውጀው ድንገተኛ የለውጥ ሰደድ በየካቲት 66 ግም ሲል፣ ልቡ በቅጽበት በደስታ ተሞልቶ፤ ነፍሱ የማይታሰብ ነገር እንዴት ተደርጎ በማለት የቆዘመበት ወቅት እንደነበር ብዙም ያልራቀ ትዝታችን ነው።

በወቅቱ ምዝብር የኢትዮጵያ ላብ አደሮች መረን የለቀቀ የመብት ጥሰት ማለትም ጉልበትን እጅግ በርካሽ ዋጋ መሸጥ፤ አስተማማኝ የሆነ የሥራ ዋስትና አለመኖር፣ ጤናን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችለውን ሥራ ካለ ዋስትና ለመሥራት መገደድ፤ በቂ ህክምናን አለማግኘት፤ ከሥራ ተመጣጣኝና ተገቢ የደሞዝ ጭማሪ አለመኖርና የመሳሰሉት በደሎች ይደርሱባቸው ነበር። ይህንን ለማስወገድና የሠራተኛውን መብቶች ለማስከበር በሠራተኛው ቁጥጥር ሥር የሆነ ነፃ የሠራተኛ ማኀበር ለማቋቋም እንዳይችሉም ታግደው አበሳቸውን ቆጥረዋል። በየካቲት 66 ይህን አስከፊ ሁኔታ ለአንዴም ለሁሌም ለመለወጥ የሚችል የተስፋ ደወል በመላ ሃገሪቱ አስገመገመ። ይህ ደግሞ ለዚያን ጊዜዎቹ ላብ አደሮች፣ በርግጥም ትግላቸው አብቦ ሊያፈካ የመቃረቡን ዕውነታ የወርሃ የካቲቱ የለውጥ ነፋስ "አበራ የተከልከው ዘር አፈራ..." እያለ በድንገት ሹክ ባለበት ጊዜ ድቅድቁ የጨለማ ዘመን ማብቂያው ገና በውል ባይታወቅም፣ ነገር ሁሉ ግን እንደወትሮው የመቀጠሉ ያበቃለት ምዕራፍ ላይ መድረሱን አበሰራቸው። ይህም "ብርሌ ከነቃ ..." እንዲሉ መሆኑን ያመላከተ በመሆኑ ላብ አደሩ በብሩህ ተስፋው ወደፊት ያማተረበትና የረጅም ጊዜ ትግሉን እዳር ለማድረስ የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ መግባቱን ያጤነበት እንደነበር ዛሬም በሕሊናችን የታተመ ዕውነታ ነው።

የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት የኢትዮጵያ ሴቶች የጉልተኛው ሥርዓት ውጤት የሆነው የወንድ ማን አህሎኝነት ያደርስባቸው በነበረው የከፋ በደል እጅጉን የተጎዱ ነበሩ። ከዚያም ባሻገር የፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ አስከፊ ተጽዕኖዎች ሁሉ ሰለባ ሁነው፤ የቤተሰብ ማገርና መሠረት የመሆናቸው ታላቅ ሚና ተገቢውን ዋጋና ክብር አጥቶ፤ በምትኩ ሴት በመሆናቸው ብቻ በኅብረተሰቡ ውስጥ የድርብ ጭቆና ሰለባ ሆነው ፍዳቸውን ሲያዩ ኖረዋል። ይህን በሚያዩበት በዚያ ዘግናኝ ሥርዓት ውስጥ፣ የነበሩበትን አስከፊ ሁኔታ ዕድሜ የሚያሳጥር ሁኔታ መቃረቡን ባልጠበቁበትና ባልጠረጠሩበት ሰዓት ወርሃዊ የካቲት ስድሳ ስደስት ሊያበስራቸው የምስራቹን ይዞ

ከተፍ ሲል፣ "ምስር ብላ!" ያሉበት ያ አስደሳች ቀን ወቅቱን ለኖረው ሁሉ በርግጥም ትናንትና የሆነ ይመስላል - በሰላሳ ሰባት ዓመቱ።

ትኩስ ጉልበቱን ለጋ ህይወቱን ለአብዮቱ ያለው የኢትዮጵያ ወጣት የየካቲቱ አብዮት፣ እንደተቀረው ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ፈጥኖ ደራሽ ይሆናል ብሎ ባልገመተው ወቅት ነበር እንደ እንግዳ ደራሽነትና እንደ ዉሃ ፈሳሽነት ተውኔት ከፊቱ የተደቀነው። ወጣቱ በራሱም ላይ ይሁን በተቀረው ሕዝብ ላይ ሲደርሱ የነበሩትን ቅጥ ያጡ በርካታ ግፍና በደሎች እንዲወገዱ ቀደም ሲል ተቃውሞውን በመደጋገም አሰምቷል። የሥርዓቱን ብልሹነትና ኢፍትሃዊነት አጋልጧል። ለእስራት፣ ለስደት የዳረገውንና ብሎም ህይወትን ያስከፈለውን ትግል ሲያደርግ ቆይቷል። እነጥላሁን ግዛው፣ እነ ዋለልኝ መኮንንንና ሌሎች በርካታ ተራማጅ ወጣቶች ለትግሉ ህይወታቸውን ከፍለዋል። በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ያበቀለችው ወጣቱ ትውልድ የህዝብና የሀገር ፍቅር በልቡ ውስጥ እንደ አሳት እየነደደ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ጀግና ትውልድ ለመሆኑማ ምን አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። በድንገት የደረሰው የየካቲት የለውጥ ሞገድ ይህን ወጣት ከፍል ከማንም በላይ የመንፈስ ፍሰሃ ውስጥ ከትቶት እንደነበር ኋላ በሂደቱ የተጓዘባቸውና ያከናወናቸው ታላላቅ ቁም ነገሮች ምስክሮች ናቸው፡፡ እናም ዛሬ የካቲት ሲታወስ ሁሉም የተገፉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ ያችን ላጭር ጊዜም ቢሆን የተቋደሷትን፤ መልካም ተስፋንና ብሥራትን የፈነጠቀችውን ወቅት መለስ ብለው በሃሳብ የሚያስቧት የሚቆዝሙባት መሆኑ ግልጽ ነው።

ሌሎችም በማንነታቸው፣ በቋንቋቸው፣ በባህላቸው በእምነታቸው የተነሳ በገዛ አገራቸው እንደባይተዋር ተቆጥረው ሁሌም ፍትህ ርትዕ ተጓድሎባቸው ያላሰለሰ በደልና ግፍ ሰለባ ሆነው አንገታቸውን አንዲደፉ የተደረጉባት አገርም ነበረች ብንል የነበረውን ዕውነታ መናገራችን ነው። ለነዚህም የህብረተሰቡ ክፍሎች ድንገት ሳይታሰብ፣ ይህን የኑሮ ሁኔታቸውን በሌላ በተሻለ ለመለወጥ የሚያስችል ቀን መቃረቡን የሚያበስር የለውጥ ደወል በመላ አገሩ ሲያስተጋባ ለዘመናት ሲጓጉለትና ሲመኙት የቆየው፣ የቋንቋቸው መከበር፣ በባህላቸው የመኩራት፣ እምነታቸው ተገቢውን ክብር የማግኘት፣ ...ወዘተ የቱን ያህል ልባቸውን በደስታ ሞልቶት እንደነበር እስከዛሬም የሚናገሩት ሐቅ ነው።

ግና ወርሃዊ የካቲት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩትን ምዝብር ሕዝቦች ያስፈነደቀውን ያህል፣ ኢትዮጵያ ግን ተስፋቸውንና ጽኑ ፍላጎታቸውን እዳር ለማድረስ የሚያስችል ብቃትና ዝግጅት የነበረባ ት ሁኔታ ውስጥ አልነበረችም። እንዲሁም፣ ምንም እንኳን ሁኔታውን ቀድመው የተረዱ ዜጎች የነበሩት ቢሆንም፣ ራሱን በበቂ አደራጅቶና ጎልብቶም የሕዝባዊውን እንቅስቃሴ የሚያቀነባብርና አቅጣጫ የሚያስይዝ ብሎም እራሱን ይፋ ያረገ መሪ ድርጅት አልነበራትም። እንዲያም በመሆኑ ወቅቱ ተስፋን በሚገድሉና ብሩሁን በሚያደበዝዙ አጥፊ ኃይሎችም ጭምር የታጀበ ስለነበር፣ እንቅስቃሴው

ያነጣጠረበትን ሥርዓት ሲያገለግሉ የቆዩ ጥቂት ወታደሮች አጋጣሚውን በመጠቀም፣ በለውጥ ሐዋርያነት ስም ራሳቸውን ሰይመው በሂደቱ ላይ ጋሬጣ ሆነው ቆሙ። ታስረው የነበሩ እጆች፣ ተሸብበው የቆዩ አንደበቶች፣ ታምቀው የከረሙ ልዩ ልዩ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች እንደልባቸው የሚገኙበት፣ ያሻቸውን የመቀበል ያልፈለጉትን የመተው መብት የተከበረበት... ወዘተ ሁኔታ ላጭር ጊዜም ቢሆን በመላ ምድሪቱ አበራ። የማንበብ የመጻፍ፣ የመወያየት የመከራከር ወዘተ....ባህል ባንድ አፍታ ገዝፈው ከቶውንም የሚናፍቁና ጭራሽ የማይጠገቡ ተውኔቶች ሆኑ። ግና ብዙም ሳይቆዩ ገና በእንጭጭነታቸው ድክ ድክ ብለው እንዲከስሙ ተደረጉ። ይህን ሁኔታ ነበር ኢሕአፓ የየካቲት የለውጥ ሂደት ካስገመገመ ከአስራ አራት ዓመታት በኋላ በልሳኑ በዴሞክራሲያ ቅጽ14. ቁ1. የካቲት 1980 እትሙ የሚከተለውን ያሰፈረው።

"አንደ እንግዳ ደራሽ፣ አንደውሃ ፈሳሽ፣ አአምሮ ባልገመተው፣ ልቡና ባልጠበቀው ሰዓት የካቲት ግም ሲል፣

- -ፊውዳሊዝም ይውደም፣
- -አምፔሪያሊዝም ይውደም፣
- -መሬት ለአራሹ፣
- -ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጨቅኖች ያለገደብ፣
- -ብሄሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት ይከበር፣
- -ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም...ወዘተ

የሚሉ ንውዳን መፈክሮች፣ ከእሳት ላንቃዎች እንደትንታግ በመወርወር የምዝበራና የምንዳቤ ኃይላትን ለማጋየት ወላፈናቸውን ከጫፍ አስከ ጫፍ ሲወረውሩ የየካቲት የጽንሰቱ ብሥራት ከምድር አስከ አርያም ተሰማ። ዓመታት እየተንኳተቱ አንድ ሱባኤ ጨርሰው ሁለተኛውን ሱባኤ ያገባዱ እንጂ የካቲት በአቢይ ኃይልና ሥልጣን ራሱን ከሥቶ ለኢትዮጵያ ምንዱባንና ምዝቡራን ይዞላቸው የመጣው መልክት ገና አልደረሳቸውም።

ከኢትዮጵያ ህዝብ ብካይና ሰቆቃው፣ ረሃብና ቀጠና የተጸነሰው የካቲት ገና አልተወለደም፤ የሰው ልጅ እንደ እስትንፋሱ በነሲብ ሊያገኛቸው የሚገቡ - ህልው ከመሆን ጋር የማይነጣጠሉ - የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ፅጋዎቹ እስከተነፈጉት ድረስ የካቲት ከተረገዘበት ማህጸኑ አይወጣም፤ እውነተኛውና ቁርጠኛው የካቲት ይወለድ ዘንድ ብዙ ጻማ፣ ብዙ ጋር፣ ብዙ ጣር ያስፈልጋል፤ የካቲት ተወልዶ አገር ላጡት አምባ መጠጊያ፣ ለተገፉት ጋሻ መከታ፣ ይሆን ዘንድ እነዚያ የካቲት ሲጸነስ የተነሱት መሠረታውያን ጥያቄዎች ነፍስ ነስተው በግዘፈ ሥጋ መከሰት ይኖርባቸዋል።"

ግና ያ አልሆነም። በምትኩ በራሱ ውስጥ በርካታ ባይሆኑም ቀና አመለካከት የነበራቸውን እያደባ መንጥሮ ሙሉ በሙሉ አምባገነንነቱን የተጎናጸፈው ወታደራዊ ቡድን፣ የሕዝቡን እንቅስቃሴ ከማገዱና ከመቀልበሱም በላይ፣ በታሪክ የውጭ ጠላት እንኳን ያላደረሰውን ዘግናኝና አረመኔያዊ ግፍ ፈጸመ። አንድ ትውልድ እንዳለ መተረ፤ በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ጥሮ፣ ብዙ ከፍሎ በእውቀት ኮትኩቶ ያሳደጋቸውን፣ ሀገር አፍቃሪ ተኪ የማይገኝላቸውን፣ ለእድገቷ ቁልፍ ሚናዎችን ሊጫወቱ ይችሉ የነበሩትን ብርቅዬ ልጆች እንደዋዛ አጣ። ምድሪቱ በየካቲት ስድሳ ስድስት እልል እንዳላለች ሁሉ ባጭር ጊዜ ውስጥ ከል እንድትለብስ ተደረገች። እዬዬና ዋይታ በየቦታው ሆነ። መረን የለቀቀው ፋሽስታዊ በትር እጅግ በጣም ዘግናኝ ስለነበር፣ እስከ ወዲያኛውም ጠባሳው የማይሽር የስነ ልቦና ቀውስ እንዲረምም አደረገ። አገር አሥራ ሰባት አመት ሙሉ የሽብርና የትርምስ ሰለባ ሆና ስትናውዝ ከረመች፤ የሲኦል የፍዳ ዘመን ሆነች። ከዚህም በላይ ፋሽስታዊው ቡድን በስፋት ያካሄደው አረመኔያዊ ድርጊት ሃገርን ሆን ብለው ለማጥፋት ይንቀሳቀሱ ለነበሩ ኃይላት ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸውና ዓላማቸውን ከግብ እንዲያደርሱ ምክንያት ሆኖ የአገር ህልውና አደጋ ላይ ሊወድቅ ቻለ።

አ የካቲት! ዛሬም በማህጸን ውስጥ እንዳለ ሌላ ሃያ ዓመታትን አስቆጠረ። አገራችንና ሕዝባችን ዘረኛና ከፋፋይ፣ ጸረ ኢትዮጵያ በሆነ ጠባብ ቡድን ሥር በከፍተኛ ደረጃ እየተሰቃየ ይገኛል። መብቱ ተገድቧል። ታፍኗል። የአንድ ዘር የበላይነት ነግሷል። ህዝባችንን በዘርና በጎሳ ለመከፋፈል የተጀመረው ተንኮል በተለያየ መንገድ ቀጥሏል። ረሃብ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት በየዓመቱ በሚጎበኝበት ሁኔታ፣ ኤኮኖሚው አደገ፣ ተመነደገ እየተባለ ይደለቃል። የሀገራችን ሃብት ጊዜ ሰጥቷቸው ሥልጣን ላይ በተቀመጡ ጉዶች እየተዘረፈ ነው። የአገራችን ለም መሬትም ለባዕዳን እየተቸበቸበ ነው። የትምህርት ይዘታው ወድቋል፤ በሽታዎች ተስፋፍተዋል። ባጠቃላይ ከሚንደላቀቁት ጥቂቶች በስተቀር ሃገሪቱ ለብዙሃኑ ሲኦል ሆናለች ብንል ማጋነን አይሆንም።

ያም ሆኖ ላለፉት ሰላሳ ሰባት አመታት ሕዝባችን የፋሽስታዊውን ሆነ የዘረኛውን ከፋፋይ ቡድን ሲታገል ቆይቷል። አሁንም ጭምር እየታገለ ነው ያለው። ግና በዚሁ ሂደት ትግሉ ሊቀዳጀው የሚገባውን ዋናና መሠረታዊ ጉዳይ ፣ ማለትም ይህን ዘረኛ ከፋፋይ ቡድን፣ ኢትዮጵያን እያጠፋ ያለን እብሪተኛ ኃይል በጠላትነት ፈርጆ ለውድቀቱ መፋጠን ባንድ የመትመሙ ጉዳይ አንድም በራሱ በዘረኛው ቡድን የሰርጎ ገብነት ደባ አሊያም በየምዕራፉ ብቅ በሚሉ በሕዝብ ትግል ላይ ውሃ በሚያፈሱ ተንበርካኪዎች እየተደናቀፈ እነሆ እዚህ ደርሷል። ወያኔ ሙሉ በሙሉ በሕዝብ የተጠላ ኃይል ነው። በሥልጣን ለመቆየቱ ጠንካራ ኃይል ያለመኖርና የተቃዋሚው መዳከም ብቻ ነው ሰበቡ። ይህ ግን ወጣም ወረደ አስከወዲያኛው እንዳለ የሚቀጥል አይሆንም። ዛሬ የዓለምን ሁሉ ሕዝብ ዐይንና ጆሮ የሳበውና በሰሜን አፍሪካና በመከካለኛው ምስራቅ ባሉ አምባገነኖች ላይ ያነጣጠሩትን

ሕዝባዊ አመጾች (የቱኒዚያው፣ የግብጹ፣ የየመኑ፣ የባህሬኑ፤ የጆርዳኑ...)፤ የተነሱትን ጥያቄዎች፤ እንዲሁም ለዓመታት በነዚህ የተለያዩ ሀገሮች ሕዝቦች ላይ አምባገነኖች ያደረሱባቸውን በደሎችና ግፎች ከኛው በሽታዎች ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነት ስናጤን ዳግም የካቲት በኢትዮጵያችን የመወለጃው ተስፋ እያንሰራራ መሆኑን ማማተራችን አልቀረም። ይህን ስንል ግን አጠቃላዩን ሁኔታ የሚመሳሰሉበትን ለመጠቆም እንጂ ለሁኔታው መከሰት የየሃገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ወሳኝነቱ የሚዘነጋን አይሆንም።

በመሆኑም ዛሬ ይህን ዘረኛና ከፋፋይ፣ ኢትዮጵያን እየገደለ ያለን ጠላት የማስወገዱ ላይ ቁርጥኝነቱ ያላቸው ሁሉ ዳግም የካቲት በኢትዮጵያ ምድር ይናኝ ዘንድ ልዩነታቸውን አቻችለው፣ ድክመታቸውን አውቀውና አርመው፣ የዘረኛውን ቡድን ውስብስብ ከፋፋይ ሴራ በጣጥሰው በመካከላቸው ንፋስ እንዲገባ እየተሸረቡ ያሉትን ተንኮሎች ሁሉ እያከሸፉ፣ በደከሙበት እየጎለበቱ፣ በጠነከሩበት ይበልጥ እየገፉ ትግላቸውን እያቀናጁ የመጓዛቸው አስፈላጊነት ከምንጊዜውም በላይ ዛሬ እንደሆነ የሚታይ ነው። ከሌሎች ሕዝቦች ትግልም ሆነ ከራሳችንም የካቲት 66 አያሌ ጠቃሚ ትምህርትን ቀስመን በሥልጣን ላይ ሲባልግ የቆየውን ዘረኛ አገዛዝ ውድቀት ማፋጠንም ይጠበቅብናል።

ዳግም የካቲት ይወለዳል!!
ጻረ ወያኔው ትግል ይፋፋማል!!